# የኢኮቴ መሰረተ ልማት አቅርቦትና አገልግሎት የስራ ሂደት

1. የኢኮቴ ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች

## 1.1 ራዕይ

የህዝባችንን ህብረተሰባዊና ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማሻሻል በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም የሚፈጠሩትን ምቹ ሁኔታዎች በመጠቀም በዞናችን ቀጣይነት ያለው ማህበረሰባዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት እንዲሁም ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር ሰፍኖ ማየት፤

## 1.2 ተልዕኮ

በዞናችን የልማት እንቅስቃሴ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም አቅምን በማጎልበት የክልላችንን ማህበረሰባዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት የበለጸገ እንዲሆን ማድረግ፤

## 1.3 እሴቶች

- ውጤታችንም ሆነ ውድቀታችን የጋራችን ነው
- በጋራ እንማማራለን
- የተገልጋዮቻችን ችግር ፈቺዎች ነን
- ስራችንን በታማኝነት እንፈጽማለን
- ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ጥራትና ወጪ ቆጣቢ አገልግሎት እንሰጣለን
- መረጃ ሃብት ነው

## 1.4 የሚሰጣቸው አገልግሎቶች

- ❖ እንደ እርሻ፣ጤና ትምህርት ለመሳሰሉትና ቅድሚያ የተሰጣቸው ዘርፎች በኮምፒዩተር የታገዘ የመረጃ ስርኣት እንዲኖራቸው ኔትዎርክ መዘርጋት
- ❖ በመንግስት ተቋማት ያሉ መረጃዎች (ዳታቤዝ ማቋቋም የመረጃ ቃትና ድህረ-ገጽ) ተደራጅተውና ተቀናጅተው በጥቅም ላይ የሚውሉበትን ዘዴ እና ስነስርአት ማበጀት፡፡
- ❖ የቪዲዮ ኮንፈረንሲንግ አገልግሎት መስጠት፡፡
- ❖ በኢኮቴ ዙሪያ የሰው ሃይል ስልጠናና የምክር አገልግሎት መስጠት
- ❖ የገጠሩን ህብረተሰብ የመረጃ መረብ ቴክኖሎጂ አገልግሎት እንዲያገኝ ማስቻል

- የሴቶችና አካል ጉዳተኞች የሚያጎለብት መረጃ መረብ ቴክኖሎጂ ስርአቶችና ፕሮግራሞች መደገፍ
- የኢኮቴ መሳሪያዎች ጥገና ማካሄድ

### 1.5 የስራ ሂደቱ ግብዓት፣ ተግባራትና የሚጠበቁ ውጤቶች

| የስራ ሂደቱ ግብዓት (INPUT) | የሚከናወኑ ተግባራት (PROCESS) | የሚጠበቅ ውጤት (OUTPUT) |
|---|---|---|
| **የዘመናዊ መረጃ ልውውጥ ፍላጎት ወይም ክፍተት** | 1. የመረጃ ልውውጥ ፍላጎት ወይም ክፍተት መለየት<br>2. ዕቅድ ማዘጋጀት<br>3. ዝርጋታና ተከላ ማካሄድ<br>- መለስተኛ ሃርድዌር ዝርጋታና ሶፍትዌር ዴቨሎፕመንት<br>4. ስልጠና መስጠት<br>- መሠረታዊ የኮምፒዩተር ስልጠና መስጠት<br>5. ጥገናና ሌሎች አገልግሎቶች<br>- መለስተኛ ጥገና<br>- የምክር አገልግሎት<br>- የቪዲዮ ኮንፈረንሲንግና ሌሎች አገልግሎቶች<br>6. ድጋፋዊ ክትትል | **የተጠናቀረ ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት** |

## 2. የስራ ሂደቱ ዓላማ

### 2.1 አጠቃላይ ዓላማ

ዞናችንና የዞናችን ህብረተሰብ ካለው በግብርና ላይ ከተመሠረተ ኢኮኖሚ ወደ ዕውቀትና መረጃ ታግዞ ኢኮኖሚ እና ህብረተሰብ ለመቀየር የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዋናው መዘውሩ በማድረግ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓቱን ፈጣንና ቀልጣፋ በማድረግ መልካም አስተዳደርንና ዲሞክራሲ ማስፈን ነው፡፡

### 2.2 ዝርዝር ዓላማ

- ኢኮቴን ከፍተኛ የኢንዱስትሪና የዕድገት መሠረት እንዲሆን ማስቻል

- የዞናችንን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ለማፋጠን ኢኮቴን እንዲስፋፋ አስፈላጊውን ሁኔታ ማመቻቸት
- የሲቪል ሰርቪሱን አገልግሎት ዘመናዊ በማድረግ የአገልግሎት አሰጣጡን ቀልጣፋ እንዲሆን እና ብክነትን ለመቀነስ ብቁና የሰለጠነ የሰው ኃይል መገንባት
- የገጠርና የከተማን ተራክቦ (Connectivity) በማጎልበት ሁለቱም ላለማቀፉ የመረጃና የመገናኛ መሠረተ ልማት መረብና አገልግሎት ያላቸውን ቅርበት ማጠናከር
- በዞኑ የሚገኙ ህብረተሰብ በየደረጃው ለሚገኙ የመንግስት አካላት ውስጣዊ ግንኙነት በኤሌክትሮኒክስ የታገዘ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ጠንካራና እንደሁኔታው ሊጣጣምና ሊያድግ የሚችል መረጃና የመገናኛ መሠረተ ልማት መዘርጋት
- ስለ ኤሌክትሮኒክስ ንግድና ግብይት ጥቅም በህብረተሰቡ ውስጥ ግንዛቤ መፍጠር

## 3. ተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት ፍላጎቶች

| ተገልጋዮች | ባለድርሻ አካላት | ፍላጎቶች |
|---|---|---|
| ➢ የዞኑ መንግስትና በየደረጃው ያሉ የመንግስት ተቋማት<br>➢ ሕብረተሰቡ | • የዞኑ መንግስት<br>• ቴሌ ኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን<br>• ትምህርት ሚኒስቴር<br>• የክልሉ አቅም ግንባታ ቢሮ<br>• ትምህርት መገናኛ ዘዴዎች<br>• ፌዴራል ኢኮቴ ኤጀንሲ | ➢ ቀልጣፋ የኢ.ኮ.ቴ መሠረተ ልማት ዝርጋታና የማስፋፋት ስራዎች በአፋጣኝ እንዲከናወን<br>➢ ብቃት ያለው፣ ወቅታዊና ተከታታይ ስልጠና<br>➢ ጥራት ያለው ፈጣን የጥገና አገልግሎት እንዲሰጥ<br>➢ ተከታታይነት ያለው ድጋፍና የምክር አገልግሎት<br>➢ በተዘረጉ የኢ.ኮ.ቴ መሠረተ ልማቶች የተሟላና ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲሰጥ |

4. **የስራ ሂደቱ ከሌሎች የስራ ሂደቶች ጋር ያለው ግንኙነትና ተመጋጋቢነት፡-**

የስራ ሂደቱ ሌሎች የስራ ሂደቶች የመረጃ ልውውጣቸውንና አጠቃላይ ስራዎቻቸውን ቴክኖሎጂን በመጠቀም ቀልጣፋና ዘመናዊ በሆነ መንገድ ማከናወን እንዲችሉ ፍላጎቶችን በማጥናትና ከየስራ ሂደቱ የሚቀርቡ አገልግሎት ጥያቄዎችን መሠረት በማድረግ፡፡

- የኢኮቴ መሠረተ ልማቶችን /Hardware and Software/ እንዲዘረጋ ያደርጋል፡፡
- መሠረታዊና አድቫንስድ) አገልግሎት ከአንድ ማዕከል እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡
- ለሌሎች የስራ ሂደቶች መለስተኛ የጥገና አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡
- የምክርና ድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

5. **የስራ ሂደቱ ተግባርና ኃላፊነት**




- ✯ በስሩ ለሚገኙ ሴክተር መ/ቤቶች መለስተኛ የኢኮቴ መሠረተ ልማትና ዝርጋታ ያከናውናል::
- ✯ በክልሉ በሚዘጋጀው ማኑዋል መሰረት መሠረታዊ የኮምፒዩተር ዕውቀት ስልጠና ለዞን ሴክተር መ/ቤቶች ይሰጣል
- ✯ በዞን ሴክተር መ/ቤቶች የሚገኙ የኢኮቴ መሣሪዎች ብልሽት ሲኖር መለስተኛ ጥገና አገልግሎት ይሰጣል፡፡
- ✯ አስፈላጊውን የኮንፊገሬሽን ስራ በማካሄድ Point to Point የቪዲዮ ኮንፈረንሲንግ አገልግሎት ይሰጣል::
- ✯ የዳታ፣ የኢሜይል፣ የዳይሬክተሪ፣ የድምጽና የኢንተርኔት አገልግሎቶች ይሰጣል::

- ✯ ለዞን ሴክተር መ/ቤቶችና በስሩ ለሚገኙ ወረዳዎች ድጋፋዊ ክትትል ያደርጋል::
- ✯ ስራውን በተመለከተ በየወቅቱ ለሚመለከተው ክፍል ሪፖርት ያደርጋል
- ✯ በየደረጃው ላሉ አካላት ስራውን በተመለከተ ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል::

## 6. የአገልግሎት ቅድመ ሁኔታ

- **የኔትዎርክ ዝርጋታ አገልግሎት ቅድመ ሁኔታ**
  - በዕቅድና በበጀት የተደገፈ መሆን አለበት
  - በተቋሙ ስራውን ሊከታተልና ሊረከብ የሚችል ባለሙያ ሊኖረው ይገባል
  - በደብዳቤ የአገልግሎት ጥያቄውን የበጀት ዓመቱ ከመጀመሩ 3 ወር ቀደም ብሎ ማቅረብ
- **ለመለስተኛና አድቫንስድ ስልጠና ቅድመ ሁኔታ**
  - የሚያሰለጥነውን የስልጠና ዓይነት ለይቶ ማቅረብ አለበት
  - የሰልጣኞችን ብዛት ማሳወቅ
  - የስልጠና ወቅት (ጊዜ) ማሳወቅ
  - ለአድቫንስድ ስልጠና መሠረታዊ የኮምፒዩተር ክህሎት ያላቸው መሆን ይገባቸዋል
  - ሰልጣኞች በተቋማቸው ኮምፒዩተር ያላቸው ብቻ መሆን አለባቸው
- **የጥገና አገልግሎት ቅድመ ሁኔታ**
  - ከተቋማቸው የድጋፍ ደብዳቤ ማምጣት
  - ስለብልሽቱ አጭር መግለጫ ማቅረብ
  - የጥገና ጥያቄ ማቅረቢያ ፎርም መሙላት
- **የቪዲዮ ኮንፈረንሲንግ አገልግሎት ቅድመ ሁኔታ**
  - ፕሮግራሙ ከመካሄዱ 7 ቀን ቀደም ብሎ ማሳወቅ
  - የተሳታፊዎችን ብዛት ማሳወቅ
  - የማዕከሎቹን ብዛት ማሳወቅ
  - አገልግሎቱ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚካሄድ ማሳወቅ
- **የሶፍትዌር ዴቨሎፕመትን አገልግሎት ቅድመ ሁኔታ**
  - በተቋማቸው ኔትዎርክ መኖሩን ማረጋገጫ ማቅረብ
  - አጠቃላይ የተቋሙን መረጃ የያዘ ሰነድ ማቅረብ

- ስራውን የሚከታተልና የሚቆጣጠር እንዲሁም ተረክቦ ስራውን ሊያስቀጥል የሚችል ባለሙያ ሊኖረው ይገባል
- የአገልግሎት ጥያቄውን በደብዳቤ ማቅረብ

- **የድጋፍና ምክር አገልግሎት ቅድመ ሁኔታ**
  - ጥያቄውን በስልክ፣ በኢሜይል፣ ፋክስ ወይም በደብዳቤ ማቅረብ
  - የሚፈልጉትን ድጋፍና ምክር አገልግሎት ዓይነትና ስፋት በግልጽ ማሳወቅ

*መግለጫ*

1. **መለስተኛ ኔትወርክ** ፤ማለት 10 ኮምፒውተርና ከዚያ በታች የሆኑ ኮምፒተሮችን የማገናኘት ስራና ፕሪንትርና ፋይል ሼር የማድረግ ስራን እንዲሁም በአንድ ፍሎር የሚካሄድ የኬብሊንግና ክሪፒንግ ስራን ያከትታል ፡፡
2. **ውስብስብ (ከባድ ኔትወርክ ዝርጋታ)** ፤ማለት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ የኔትወርክ ዝርጋታዎች፤የገመድ አልባ ኔትወርኮች የኮኒፍገሬሽን ስራ ያላቸው የራውተርና ስዊች የቪዲዬኮንፈረንስ ተከላ ስራን የካትታል ፡፡
3. **መለስተኛ ጥገና** ፤ማለት የኮምፒውተር ሃርድ ዌር መቀየር የሶፍትዌር መጫን፤
4. **ከባድ ጥገና** ፤ማለት የኮምፒውተርና ተዛማጅ መሳሪያዎች ሃርድዌር ጥገና፤የስኩልኔት መሳሪያዎች :የወረዳኔት እቃዎች ጥገና ፤የፕሪተርና ፎቶኮፒ የፋክስ ማሽን ጥገና ፡፡

7. **ድጋፋዊ ክትትልና የግምገማ ስርዓት**

- አስፈላጊውን የድጋፋዊ ክትትል ቼክ ሊስትና ፕሮግራም ለመንደፍ በየደረጃው ላሉ የመንግስት ተቋማትና የህብረተሰብ አካላት ለተቋቋሙ ወይም ለተዘረጉ የኢኮቴ መሠረተ ልማቶች በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውሉና ቀጣይነታቸውን ለማረጋገጥ ተከታታይ የሆነ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡ የክትትልና ድጋፍ አፈጻጸም ሂደቱም በየደረጃው በመስክ በዓመት 2 ጊዜ ጉብኝት በማድረግ፣ የመስመር ላይ አገልግሎት ወይም (Online Service) በመጠቀም፣ ሪፖርቶችን በመገምገምና ግብረመልስ በመስጠት ይካሄዳል፡፡
- በስራ ሂደቱ አፈጻጸም ዙሪያ በሳምንት 1 ጊዜ ተሰብስቦ ግምገማ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ግን አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥም የሂደቱ መሪ በማንኛውም ጊዜ አጠቃላይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

- የቲም አባላት በተመደቡበት ስራ አፈጻጸም ዙሪያ ሳምንታዊ፣ ወርሃዊ፣ ሩብ ዓመት፣ የግማሽ ዓመትና ዓመታዊ የጽሁፍ ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡ በሂደቱ አባላትም ውይይት ይደረግበታል፡፡